የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ — ነሐሴ ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st Year No. 3
ADDIS ABABA – 22nd August, 1995

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፹፯ ዓ.ም.
የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ .......... ገጽ ፵፩

## CONTENTS

Proclamation No. 3/1995
Federal Negarit Gazeta Establishment
Proclamation ............................................... Page 41

## አዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፹፯

## የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣን ማቋቋም በማስፈለጉ ፤ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፹፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ መቋቋም

፩· የፌዴራል የሕግ ጋዜጣ የሆነ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የሚወጣ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት ሕግ የሚወጣው በፌዴራሉ ነጋሪት ጋዜጣ ይሆናል።

፫· ማናቸውም የፌዴራል ወይም የክልል ህግ አውጪ ፣ አስፈጻሚ እና ተርጓሚ እንዲሁም ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጣ ሕግን የመቀበል ግዴታ ይኖርበታል።

፬· የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ የሚታተመው በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ይሆናል፤ በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል የይዘት ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ የአማርኛው የበላይነት ይኖረዋል።

## PROCLAMATION NO. 3 / 1995

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE FEDERAL NEGARIT GAZETA

WHEREAS, it has become necessary to establish the Federal Negarit Gazeta;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as folows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the ''Federal Negarit Gazeta Establishment Proclamation No.3/1995''.

2. *Establishment of the Federal Negarit Gazeta*
   1. The Federal Negarit Gazette, a Federal Law Gazette published under the Umbrella of the House of Peoples' Representatives, is hereby established.
   2. All Laws of the Federal Government shall be published in the Federal Negarit Gazeta.
   3. All Federal or Regional legislative, executive and judicial organs as well as any natural or juridical person shall take judicial notice of Laws published in the Federal Negarit Gazeta.
   4. The Federal Negarit Gazeta shall be published in both the Amharic and English Languages; in case of discrepancy between the two versions the Amharic shall prevail.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 1·20

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· <u>የተሻረ ሕግ</u>

የነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፴፬ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም

(ዶ/ር) ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

3. *Repeal*

The Establishment of the Negarit Gazeta Proclamation No.1/1942 is hereby repealed.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 22nd day of August, 1995.

Done at Addis ababa, this 22nd day of August, 1995.

*NEGASSO GIDADA (DR)*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC*
*REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ ።
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE